የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፫
አዲስ አበባ–ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 23
ADDIS ABABA-16th January, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፲/፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ለመቱ–ጐሬ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................................ ገጽ ፪ሺ፵፩

## CONTENTS

Proclamation No. 310/2003

OPEC Fund for International Development Loan Agreement for financing the Metu-Gore Road Project Ratification Proclamation .................. Page 2041

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፲/፲፱፻፺፭

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት የተደረገውን የብደር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለመቱ–ጐሬ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፬ሚሊዮን ፰፻ሺ (አራት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ) የአሜሪካን ዶላር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል እ.ኤ.አ ጁላይ ፴፩ ቀን ፪ ሺ.፪ በቪየና የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ–መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለመቱ–ጐሬ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፲/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 310/2003

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEENTHE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE OPEC FUND FOR INTERNATIONAL DEVELOPMENT

WHEREAS, a Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development stipulating that the OPEC Fund for International Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of USD 4,800,000.00 (Four million eight hundred thousand United States Dollars) for financing the Metu-Gore Road Project, was signed in Vienna, on the 31st day of July, 2002;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 16th day of January, 2003;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "OPEC Fund for International Development Loan Agreement for Financing the Metu-Gore Road Project Ratification Proclamation No. 310/2003."

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኦፔክ ፈንድ ለዓለም አቀፍ ልማት መካከል እ·ኤ·አ ጁላይ ፴፩ ቀን ፪ ሺ ፪ በቪየና የተፈረመው ቁጥር ፰፻፹፯ ፒ የብድር ስምምነት ነው።

፫· የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፬ሚሊዮን ፰፻ ሺ (አራት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ) የአሜሪካን ዶላር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር ፰ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፰ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Defintion*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. 887P signed between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the OPEC Fund for International Development on the 31st day of July, 2002.

3. *Power of the Minister of Finance and Economic Development*

The Minister of Finance and Economic Development is empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of USD 4,800,000.00 (four million eight hundred thousand United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the loan agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 16th day of January, 2003.

Done at Addis Ababa, this 16th day of January, 2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE